# የልጅ ዓብይ ጉዳይ

ለጠ/ሚኒስትር ዓብይ አህመድ (ዶ/ር)
በአባቱ ኦሮሞ በእናቱ አማራ፤
ከሙስሊም ክርሰትያን እምነት የተጋራ።
የዘር ሉጋም የለሽ ኰለኤል ወታደር፤
ኢትዮጵያዊ ዜጋ አራት ዓይና ምሁር።
ግራ ቀኝ አማትሮ፤ ሁሉን እኩል የሚያይ፤
ከአድማስ ባሻገር አርቆ አሰተዋይ፤
የሀገር ፍቅር አንድነት፤ ውል ቃል ኪዳን አዋይ፤
እናትን ማዳን ነው የልጅ ዓብይ ጉዳይ።
ኢትዮጵያ እጆችዋን ለእግዚአብሔር ዘርግታ፤
የዐሎትዋን... ምላሽ ይሰጣታል ጌታ።
እኛ ዛሬ አድድቀን፡ ነገ እንኰንናለን፤
ጠዋት ከሰቅለነው ፡ ማታ እናወርዳለን፤
ደግፈን አድንቀን..... እንቃወማለን፤
ይህ የሰው ዐባይ ነው ብንወቅስህም ቻለን።
በዚህ ቀውጢ ጊዜ ሀላፊነት ወስደህ፤
እንደ ገና ዳቦ ከታች እላይ ነደህ።
ጥንታዊት ኢትዮጵያን ወደፊት አስቀድም፤
የሰራ ይሳሳታል ማንም ፍፁም የለም፤
ዋናው ቁም ነገሩ   የጠፋው ይታረም፤
ለነቀፋ አትመች፡   እንዐልይ ለሁሉም።
ያልከውን ማድረግህን ወገን እንዲረዳ፤
የጋሪ ፈረሱን ተጠንቅቀህ ንዳ።
ወጣ ገባ አሰፓልቱ... ኮረኮንች መንገዱ፤
ዳገት ቁልቁለቱ...ጥምዝ አካሄዱ፤
የትግሉ ቀመር   ስልት ... የለማ ይሁን ገዱ፤
መስዋዕት ይጠየቃል ድል ፈርጣማ ክንዱ።
ተግሳፅና ምክር ዘለፋም... ተቀበል፤
እንደ እንዳልካቸው ፋታ፤ፋታ አትበል።
የነብሩን ጅራት ይዘህል አትልቀቅ፤
ከእጅህ እዳያመልጥ ዝናርህን አጥብቅ።
ሀገር ለማዳን፡ ወገንን ለማትረፍ፤
ምጣዱን እያየህ፡ አይጢቱ ትለፍ።
ብዙ ከመናገር፤
ጥቂት ተግባር ነገር።
ከተፎካካሪ ወይም ተቃዋሚ፤
ተግባብቶ መስራትን፡ አድርገው ተርጓሚ።
ጉልቻ ቀይሮ መተካካት ሳይሆን፤
ስር ነቀል ለውጥ አምጣ እንድንተማመን።
ዐረ አብዮት ፡ባንዳ ፡ጠባብ፡ ትምክህተኛ፤
ፋሽስት አረመኔ... ቅኝ ገዢ ዘረኛ።
ከአርባ ዓመታት ሰተት ለመማማር ካልቻልን፤
በዱሮ ትግል ስልት ዛሬም ከቀጠልን፤
ለዚህ አዲስ ትውልድ ቂምን ስናጋባ፤
እልህ   ተያይዘን ገደል እንዳንገባ።
እርቀ ሠላም አውርድ፡ የበደለም ይካስ፤
ያጠፋም ይቀጣ ፡የቀማም ይመልስ።
መሰላልን በአግባብ ረግጠው ካልተጓዙ፤
በአጉል አወዳደቅ ብዙ ነው መዘዙ።
ሁሉንም ማስደሰት አትችልምና፤
ፈተናን ለማለፍ አንገት ደፍተህ አጥና።
ፍትህ እኩልነት ሰፍኖ እንዲረጋገጥ፤
ለህዝቡ ጥያቄ ምላሽ እንድትሰጥ፤
ሞተህ ተሟሙተህ ስርዓቱን ለውጥ።
ቃል የገባህለት ሕዝባዊ ተልእኮ፤
ግብ መቶ እንዲሳካ ጀባዱ ኮርመኮ።
ከአድማስ ባሻገር አርቆ አሰተዋይ፤
ኢትዮጵያን ማዳን ነው የልጅ ዓብይ ጉዳይ።

ሽመልስ ተሊላ።
ከካናዳ።